**SIDAAMU DAGOOMU QOQQOWI MOOTIMMA AFFINI GAAZEEXA**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አፍኒ ጋዜጣ**

**SIDAAMA NATIONAL REGIONAL STATE AFFINI GAZETA**

| | | |
|---|---|---|
| 4ki Diro Kiiro 40<br>Hawaasa, Ella 8, 2016 M.D | Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Amaalete Mini Allaalshi Hundanni Fulinoho<br>በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | ፬ኛ ዓመት ቁጥር ፵<br>ሀዋሳ፣ ሰኔ ፰ ቀን ፳፻፲፮ ዓ.ም |

<u>**Amado**</u>

**Wodhote Kiiro 40/2016**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Qulxu'mete Jiro Latishshi, Gashshootinna Agarooshshi Wodho ……………… Qoola**

<u>**ማውጫ**</u>

**ደንብ ቁጥር ፵/፳፻፲፮**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የዓሳ ሀብት ልማት፣ አስተዳደርና ጥበቃ ደንብ………… ገጽ**

**Wodhote Kiiro 40/2016**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Qulxu'mete Jiro Latishshi, Gashshootinna Agarooshshi Wodho**

Qoqqowu giddo noo way bissa giddo noota jawa qulxu'mete jiro horoonsi’rate millimmo seerunnita assatenni kalaqamu jiro bikka agartino garinni ilamate sa”a hasiissannohura;

Isilaanchimma agadhino qulxu'mete laalchi shiqishsha lossatenna daganna mootimma tenne jironni afi’ra hasiissannonsa horo afi’ra noonsahura;

**ደንብ ቁጥር ፵/፳፻፲፮**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የዓሳ ሀብት ልማት፣ አስተዳደርና ጥበቃ ደንብ**

በክልሉ ባሉ የዉሃ አካላት ዉስጥ ያለዉን እምቅ የዓሳ ሀብት የመጠቀም እንቅስቃሴን ህጋዊ በማድረግ የተፈጥሮ ሀብቱ ሚዛኑን በጠበቀ መልኩ ለትዉልድ መተላለፍ ስላለበት፤

ጥራቱን የጠበቀ የዓሳ ምርት አቅርቦትን ለማሳደግና ሕብረተሰቡና መንግስት ከሀብቱ ማግኘት የሚገባቸዉን ጥቅም ማግኘት ስላለባቸዉ፤

**Mittu Waagi ….**
*ያንዱ ዋጋ*

AFFINI GAAZEEXI P.S.K …..
አኒ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. …..
Web address: www.affinigazet.gov.et

Qoqqowu Jeefisiisaanote Amaale Mini Itophiyu Federaalete Dimokiraasete Rippubilike Qulxu'mete Jiro Latishshinna Horoonsishshi lallawi Kiiro 315/95 Quwa 20 Cinaancho Quwa 2 nna Qoqqowu Bayriidi Seeri Quwa 57 cinaancho Quwa 6 garinni tenne wodho fushshino.

## Gafa Mite

## Xaphooma Woro

1. **Harancho Umo**

   Tenne wodho **"Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Qulxu'mete Jiro Latishshi Gashshootinna Agarooshshi Wodho Kiiro 40/2016"** yine woshsha dandiinanni.

2. **Tiro**

   Qaalu eo wole tiro uytannota ikka hoogguro tenne wodho giddo:-

   1. Itophiyu Federaalete Dimokiraasete Rippubilike Qulxu'mete Jiro Latishshinna Horoonsishshi Lallawi Kiiro 315/1995 aana uynoonni tiro loosu aana hossannoha ikkanno.
   2. **"Qoqqowu Mootimma"** yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimmaati.
   3. **"Biiro"** yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Saadate Jiro Latishshi Biirooti.
   4. **"Kalaqamu Akata"** yaa way bissa giddo heedhanno lubbo noonsarenna lubbo noonsakki jiro, way gamira noo mu'ronna saadda xaadooshshenna irkisama leellishanno.
   5. **"Gangalatote Qulxu'me Woshshaada"** yaa gangalatote yine mitte ikkitino

የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የዓሣ ሀብት ልማትና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር ፫፻፲፭/፺፭ አንቀጽ ፳ ንዑስ አንቀጽ ፪ እና በክልሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፯ ንዑስ አንቀጽ ፮ መሰረት ይህንን ደንብ አዉጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ **"የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የዓሳ ሀብት ልማት፣ አስተዳደርና ጥበቃ ደንብ ቁጥር ፵/፳፻፲፮"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ዉስጥ፡-

   1. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የዓሳ ሀብት ልማትና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር ፫፻፲፭/፲፱፺፭ የተሰጠዉ ትርጉም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
   2. **"ክልላዊ መንግሥት"** ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ነዉ፡፡
   3. **"ቢሮ"** ማለት የሲዳማ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ክልል እንስሳት ሀብት ልማት ቢሮ ነዉ፡፡
   4. **"ስነ-ምህዳር"** ማለት በዉሃ አካል ዉስጥ የሚኖሩ ህይወታዊና ህይወታዊ ያልሆኑ ሀብቶችን፣ በዉሃ ዳሪቻዎች ያሉ ዕፅዋትንና እንስሳትን ተያያዥነትና ተደጋጋፊነትን

manxaqqonninna nayleenete heqicho horoonsi'ratenni qulxu'me woshshaadate.

6. **“Fajjo”** yaa qulxu'me woshshaadate, daddalate woy qulxu'mete gibrinni looso ha’risate dandiisiissanno gede hajo la'annonsa mootimmate bissanni uynoonni borrote tajeeti.
7. **“Konseeshiine”** yaa mittu way bisi giddo noota qulxu’mete jiro manchoho bikkinoonni yannara sheemaatunni uynannita xawisanno.
8. **“Qulxu’me Woshshaada Hoolloonni Yanna”** yaa qulxu’mete sircho siritanno ha’rinsho agarate yine qulxu’me woshshaandannikki gede hoolloonni yanna bikka xawissanno.
9. **“Wo’ma Qulxu’me”** yaa godowire giddonni fushshinoonnikki qulxu’meeti.
10. **“Jawa Qiindille”** yaa qiidate bikkisi "0"(zeerote woroonni) 180$^{o}$c nna konni woroonni noo qiindilleeti.
11. **“Xiwantino Qulxu’me”** yaa qulxu’mete gibirinni uurrinsha giddo babbaxxino xibbi kaiminni keeraanchimmase xe'ino qulxu’meeti.
12. **“Daafantino Qulxu’me woy Horote Gobbaanni Ikkitino Qulxu’me”** yaa xaaddotennino ikko xaaddiweelo manchi beetti keeraanchimmara injaannokkirinni kisantino woy amadooshshu xe’nenni kalaqamu amado hooggino qulxu’meeti.
13. **“Zoone Tayisse Sa’anno Way Bissa Qulxu’mete Jiro”** yaa lame woy hakkuy aleenni ikkitino zoone woy woradu gashshooti tantanubbanni danna xaaddanno way bissa giddo noo qulxu’mete jiro xawissanno.
14. **“Mancho”** yaa ayee kalaqamu mancho woy seeru mannimma uynoonni bisooti.

ያመላክታል፡፡

5. **“ለመዝናኛ ዓሳ ማስገር”** ማለት ለመዝናኛ ተብሎ ልሙጥ የሆነ ነጠላ መንጠቆና የናይለን ክር በመጠቀም የሚካሄድ ዓሳ ማስገር ነዉ፡፡
6. **“ፈቃድ”** ማለት ዓሳ ለማስገር፣ ለመነገድ ወይም የዓሳ ግብርና ለማካሄድ የሚያስችል ከሚመለከተዉ መንግሥታዊ አካል የተሰጠ የጽሁፍ ማስረጃ ማለት ነዉ፡፡
7. **“ኮንሴንሽን”** ማለት በአንድ የዉሃ አካል ዉስጥ ያለዉን የዓሳ ሀብት ለሰዉ ለተወሰነ ጊዜ በዉል ማኮናተርን ያመለክታል፡፡
8. **“ለዓሳ ማስገር የተከለከሉ ወቅቶች”** ማለት የዓሳ ዝሪያዎችን የስነ-ተዋልዶ ሂደት ለመጠበቅ ሲባል ዓሳ እንዳይሰገር የተገለከለ የጊዜ ገደብን ያመለክታል፡፡
9. **“ድፍን ዓሳ”** ማለት አንጀቱ ያልወጣ ዓሳ ነዉ፡፡
10. **“ከፍተኛ ቅዝቃዜ”** ማለት የቅዝቃዜ መጠን ከዜሮ (0) በታች 180ºC እና ከዚያ በታች ማቀዝቀዝ ማለት ነዉ፡፡
11. **“የታመመ ዓሳ”** ማለት በዓሳ ግብርና ተቋም ዉስጥ በተለያዩ በሽታዎች ምክንያት ጤናዉ የተጓደለ ዓሳ ማለት ነዉ፡፡
12. **“የተበከለ ወይም የተበላሸ ዓሳ”** ማለት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ለሰዉ ጤና ተስማሚ ባልሆኑ ነገሮች የተነካ ወይም በአያያዝ ጉድለት የተፈጥሮ ይዘቱን ያጣ ዓሳ ማለት ነዉ፡፡
13. **“ዞን ተሻጋሪ የዉሃ አካላት የዓሳ ሀብት”** ማለት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የዞን ወይም የወረዳ አስተዳደር መዋቅሮችን በሚያዋስን የዉሃ አካላት ዉስጥ ያለዉን የዓሳ ሀብት ያመለክታል፡፡
14. **“ሰዉ”** ማለት ማንኛዉም የተፈጥሮ ሰዉ ወይም ህጋዊ ሰዉነት የተሰጠዉ አካል ነዉ፡፡

15. Tenne wodho giddo mitte kootemmanni xawinsoonnihu wole kootemmano amadannoho.

**3. Jeefishshu Mami-Geeshsha**

Tenne wodhora Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma giddo qulxu'me ce'nanninna latinsanni way bissa baalatenna qulxu'mete laalchi qixxaawo, tareessanna dikki'nanni qoxeessubbara jeefishshu hee'rannose.

**Gafa Lame**

**Kalaqamunna Mannu Loosino Way Bissa Giddo Heedhanno Qulxu'mete Jiro Horoonsishsha**

**4. Qulxu'me Woshshaadate Fajjo La'ano Xaphoomu Gadadishsha**

1. Daddallohonna gangalatate kalaqamu woy mannu loosino way bissanni qulxu'me woshshaadaate hasi'rannohu ayee manchino hajo la'annosi bisinni woshshaadate fajjo afi'ra noosi.

2. Xiinxalotenna buuxote loosira kalaqamu way bissanni qulxu'me woshshaadate hasi'rannohu ayee manchino biirotenni fajjo afi'ra noosi.

3. Tenne wodho garinni qulxu'me daddallohonna gangalatate woshshaadate hasiissanno tittirshu safaraano lainohunni Biiro biddissa fushshitara dandiitanno.

15. በዚህ ደንብ ዉስጥ በአንድ ጸታ የተገለጸዉ ሌላኛዉንም ጸታ ያካትታል፡፡

**3. የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ ደንብ በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዉስጥ ዓሳ በሚረባባቸው እና በሚመረትባቸዉ የዉሃ አካላት ሁሉና የዓሳ ምርት ዝግጅት ዝዉዉርና ግብይት በሚካሄድባቸዉ አካባቢዎች ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

**ክፍል ሁለት**

**በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የዉሃ አካላት ዉስጥ የሚገኝ የዓሳ ሀብት አጠቃቀም**

**4. የዓሳ ማስገር ፍቃድ የሚመለከቱ ጠቅላላ ግዴታዎች**

1. ለንግድና ለመዝናኛ ከተፈጥሮ ወይም ከሰዉ ሰራሽ የዉሃ አካላት ዓሳ ለማስገር የሚፈልግ ማንኛዉም ሰዉ ከሚመለከተዉ አካል የማስገር ፍቃድ ማግኘት አለበት፡፡

2. ለጥናትና ምርምር ስራ ከተፈጥሮ የዉሃ አካላት ዓሳ ለማስገር የሚፈልግ ማንኛዉም ሰዉ ከቢሮ ፍቃድ ማግኘት አለበት፡፡

3. በዚህ ደንብ መሰረት ዓሳ ለንግድና ለመዝናናት ለማስገር የሚያስፈልጉ ዝርዝር መስፈርቶችን በተመለከተ ቢሮዉ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

4. የዓሳ ማስገር ፈቃድን በማንኛዉም መልኩ ለሌላ ሰዉ አሳልፎ መስጠት

4. Qulxu’me woshshaadate fajjo ay garinni wolu manchira sayse aa woy umisiha ikkinokki fajjo amade qulxu'me woshshaada hoollonnite.

5. Tenne wodho garinni xiinxallotenna xiinxaawote gobbaanni ayee manchi ayee way bissanni qulxu'me woshshaadanokki gede hoollonni yannaranna dargubbara qulxu’me woshshaada hoollonnite.

6. Tenne wodho garinni ayee manchi ayee way bissanni Biirotenni woy deerru deerrunkunni noo borrote minnanni murroonni yannara woshshaadannikki gede hoollonni qulxu’mete sircho woshshaada hoollonnite.

7. Tenne wodho garinni mittu way bissira woshshadate loosira uynonni fajjo wolu way bissira horoonsi’ra hoollonnite.

8. Mittu mittunku way bisinni qulxu'me woshshaada gashshootu tantanno borro minnanni fajjinoonni woshshaandanni uduunnichi dani, batinyinna woshshaadate hayyo gobbaanni horoonsi’ne woshshaada hoolloonnite. Way bissanni qulxu’mete jiro horoonsishsha fulanno tittirshu biddissinni gumullanniha ikkanno.

9. Ayee manchi horoonsi’ranokkiha woshshaadate fajjo uytinosi uurrinshara qola noosi. Qola hoogiro fajjo horoonsi’ranni noo gede kiirranni.

10. Ayee manchino uynoonnisi woshshaadate fajjo uytinosi uurrinshubba gumultanno

ወይንም የራሱ ያልሆነ ፈቃድን ይዞ ማስገር የተከለከለ ነዉ፡፡

5. በዚህ ደንብ መሰረት ለጥናትና ለምርምር ካልሆነ በስተቀር ማንኛዉም ሰዉ በየትኛዉም የዉሃ አካል ላይ ዓሳ እንዳይሰገርባቸዉ በተከለከሉ ወቅቶችና ቦታዎች ዓሳ ማስገር ክልክል ነዉ፡፡

6. በዚህ ደንብ መሰረት ማንኛዉም ሰዉ በየትኛዉም የዉሃ አካል ላይ በቢሮዉ ወይም በየደረጃዉ ባሉ መዋቅሮች ለተወሰነ ጊዜ እንዳይሰገሩ የተከለከሉትን የዓሳ ዝሪያዎች ማስገር የተከለከለ ነዉ፡፡

7. በዚህ ደንብ መሰረት በአንድ የዉሃ አካል እንዲሰራበት የተሰጠ የማስገር ፈቃድ በሌላ የዉሃ አካል ላይ መጠቀም የተከለከለ ነዉ፡፡

8. በእያንዳንዱ የዉሃ አካል ዓሳ ለማስገር በመስተዳድሩ መዋቅር መስሪያ ቤት ከተፈቀዱ የማጥመጃ መሳሪያዎች ዓይነት ብዛትና የአሰጋገር ዘዴ ዉጪ ተጠቅሞ ማስገር የተከለከለ ነዉ፡፡ የየዉሃ አካላቱን የዓሳ ሀብት አጠቃቀም ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ በዝርዝር የሚወሰን ይሆናል፡፡

9. ማንኛዉም ሰዉ የማይጠቀምበትን የማስገሪያ ፈቃድ ለፈቃድ ሰጪዉ መስሪያ ቤት መመለስ አለበት፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ፈቃዱን እንደተጠቀመበት ይቆጠራል፡፡

10. ማንኛዉም ሰዉ የተሰጠዉን የማስገሪያ ፈቃድ ሰጪዉ መስሪያ ቤት በሚወስነዉ የጊዜ ገደብ መሰረት የወቅቱን ግብር ለግብር

yanna garinni gabbaro gamba assitanno mootimmate bissara baatino taje amadatenni umisi leelle haroonsira noosi. Way bissa giddo leeltannota qulxu’mete jiro horoonsi’rate baantanni gabbaro bikka gamba assanno mootimmate mini murro garinni ikkanno.

11. Tenne wodho garinni giddichotenna way bissanni 0.5 km geeshsha noo baatto loosidhe galtannori deerrase agartinokki woshshaado horoonsidhe barru sagalera hosannoha woshshaaddannokki gede hoolloonni way bissa qooxeessi gobbaanni fajjo afi’ra hasisukkinni barrunni 1.5 kg geeshshi qulxu’me woshshaada dandiitanno. Konni gobbaanni ayee bissa woshshaadoteno ikko wolu woshshaadate uduunnichinni daddalu hajora woshshaada hoolloonnite.

12. Xiinxallote loosira ikka hoogiro fajjinoonni woshshaadate uduunni gobbaanni fanjetenni, olu uduunninni, marzetenni, qulxu’me sammi assitanno xagganni woy elekitiriikete wolqanni ayee way bissanni qulxu’me woshshaadanna korericho way bissa aananna way qaccera amade leella hoolloonnite.

13. Ayee manchino tenne wodho quwa 8 aana worroonni garinni konseshiinete uynoonni way bissanni qulxu’me woshshaadate konseeshiine uynoonni manchiwiinni fajjo afi’ra noosi.

14. Ayee manchino fajjinoonnisi woshshaadate fajjo garinni woshshaadate fajjinoonni way bisira doyee loosira dandaanno.

ሰብሳቢዉ የመንግስት አካል የከፈለበትን ማስረጃ በመያዝ በግንባር ቀርቦ ማሳደስ አለበት፡፡ በዉሃ አካላት ዉስጥ ያለዉን የዓሳ ሀብት ለመጠቀም የሚከፈለዉ ግብር ሰብሳቢዉ መስሪያ ቤት በሚወስነዉ መሰረት ይሆናል፡፡

11. በዚህ ደንብ መሰረት በደሴቶች ላይና ከዉሃ አካላት እስከ 0.5 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የሚኖሩ አርሶ አደሮች ተራ መንጠቆን በመጠቀም ለዕለት ፍጆታቸዉ እንዳይሰገርባቸዉ ከተከለሉ የዉሃ አካላት ክልል ዉጭ የማስገር ፈቃድ ሳይዙ በቀን እስከ 1.5 ኪ.ግ ድፍን ዓሳ ማጥመድ ይችላሉ፡፡ ከዚህ ዉጪ ማንኛዉም አካል በመንጠቆም ሆነ በሌላ በማንኛዉም ዓሳ ማጥመጃ መሳርያዎችን በመጠቀም ለንግድ ማሥገር ክልክል ነዉ፡፡

12. ለምርምር ስራ ካልሆነ በስተቀር ሕጋዊ ከሆኑ የማስገርያ መሳሪያዎች ውጪ በፈንጂ፤ በጦር መሳሪያ፤ በመርዝ፤ ዓሳውን በሚያደነዝዝ ዕፅ ወይም በኤሌክትርክ ሞገድ ከማንኛውም የውሀ አካል ዓሳን ማስገርና እነዚህን ነገሮች በውሀ አካላት ላይና ዳርቻ ይዞ መገኘት የተከለከለ ነው፡፡

13. ማንኛዉም ሰዉ በዚህ ደንብ አንቀጽ 8 በተደነገገዉ መሰረት በኮንሴሽን በተሰጠ የዉሃ አካል ዓሳ ለማስገር ኮንሴሽን ከተሰጠዉ ሰዉ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

14. ማንኛዉም ሰዉ በተፈቀደለት የማስገሪያ ፈቃድ መሰረት ለማስገር በተፈቀደዉ የዉሃ ክፍል ተዘዋዉሮ የመስራት መብት አለዉ፡፡

**5. Qulxu'mete Laalcho Gamba Assanna Tareessa Lainohunni**

1. Tenne wodho garinni qulxu'mete laalcho gamba assanna hirate loosi aana bobbahino ayee manchi qulxu'mete daddalli fajjo uynoonninsa bissanni calla adha noosi.

2. Ayee manchi qulxu'mete laalcho gamba assatenna hirate loosi aana bobbahate hasirannohu loosu fajjo adhate albaanni Qoqqowu Saadate Jiro Latishshi Biironni borrotenni uynoonnisita ikkadimmate taje amada noosi.

**6. Qarqaru Agarooshshe**

1. Kalaqamunni ikko mannu loosino way bissa akati /suudi aana riico abba dandaannonna qulxu'me daafara dandaanno moola woy du'namaancho ishine way bissa giddora eanno gede assa hoolloonnite.

2. Way bissa qooxeessira heedhanno kalaqamu dubbonna muro hattonno tintanno lagganna buichubba way bissa akati amadooshshi ledo amadantinota ikkitino daafira qoxeessu baatto loosa, qaccete noo haqalenna mu'ro mura, shoqolanna giiratenni kalaqamu amadooshshe soorra hoolloonnite.

3. Konni quwi cinaancho quwa 2 worroonnihu agaramino gede hee'reenna qulxu'mete jironna wolootu way giddo heedhanno kalaqama agaranno gede dandiisiisate way qacce 0.5km woroonni shiqqi yine baatto loosa holloonnite.

**5. የዓሳ ምርት ማሰባሰብና ማዘዋወርን በተመለከተ**

1. በዚህ ደንብ መሰረት የዓሳ ምርት በመሰብሰብና በመሸጥ ተግባር ላይ የተሰማራ ማንኛዉም ሰዉ ዓሳ ለንግድ የማስገር ፈቃድ ከተሰጣቸዉ አስጋሪዎች ብቻ የዓሳ ምርት መረከብ አለበት፡፡

2. ማንኛዉም የዓሳ ምርት በመሰብሰብና በመሸጥ ተግባር ላይ ለመሰማራት የሚፈልግ ሰዉ የሥራ ፈቃድ ከማዉጣቱ በፊት ከክልል እንስሳት ሀብት ልማት ቢሮ በጽሁፍ የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ መያዝ አለበት፡፡

**6. አከባቢን ስለመጠበቅ**

1. በተፈጥሮም ሆነ በሰዉ ሰራሽ የዉሃ አካላት ሥነ-ምህዳር ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያስከትል የሚችልና ዓሳን ሊመርዝ የሚችል ደረቅ ቆሻሻ ወይም ፈሳሽ ወደ ዉሃ አካሉ ማስገባት ወይም እንዲገባ ማድረግ የተከለከለ ነዉ፡፡

2. በዉሃ አካላት ዳሪቻዎች ያሉ የተፈጥሮ ደኖችና ዕፅዋቶች እንዲሁም ገባር ወንዞችና ጅረቶች ከዉሃ አካላቱ ሥነ-ምህዳራዊ ይዘት ጋር የተያያዙ በመሆናቸዉ ዙሪያ መሬቶችን በማረስ፣ በዳሪቻዎች ላይ ያሉ ቁጤማዎችንና ዕፅዋቶችን በመመንጠርና በማቃጠል የወንዞችን የተፈጥሮ ይዞታቸዉን ማናጋት የተከለከለ ነዉ፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የዓሳ ሀብትንና በተጓዳኝ በዉሃ ዉስጥ ያለዉን የተፈጥሮ ሚዛን መጠበቅ እንዲያስችል የዉሃ ዳሪቻዎችን ከ 0.5 ኪ/ሜትር በታች ተጠግቶ ማረስ የተከለከለ ነዉ፡፡

4. Ayeeta laayyote latishsha loosate mixi'nanni latishshu loossanna pirojekite xaaddote ikko xaadiweelo laayyote heedhanno qulxu'me iima qarra abbitannokkita biirote buuxisa hasiissanno.

5. Qoqqowu giddo noo biironni fajjinoonnite gobbaanni ayee lubbo noo qulxu'mete sirchonna woloota way giddo saadanna mu'ro mittu way bisinni wole way bisira tuqisa woy tareessa hoolloonnite.

**7. Qulxu'mete Jiro Konseeshiine Aa Lainohunni**

Mittu way bisi qulxu'mete jiro qoqqowu biiro hundaasinni heedhanno tantano ledo xiinxallatenni mittu woy duuchu mannira aa dandinanni. Uuynanni danino tenne wodho loosu aana hosiisate fulanno biddissi aana gumullanni.

**Gafa Sase**

**Qulxu'me Latisa**

**8. Qulxu'mete Gibrinni Latishsha**

1. Ayee Manchi Qoqqowu giddo Qulxu'mete Sircho daddalu hajora cea hasiriro Biirootenni fajjo afi'ra noosi. Fajjo uynannihu konni woroonni xawinsoonnire wonshiro ikkanno:

a) Uurrinshate ikkado ikkitino baatto hee'rase haja la'annonsa tantano buuxo assituro;

b) Uurrinshate hassisanno ikkadu way hee'rasinna horonsi'rate injo haja la'annonsa mootimmate bissanni irko

4. በማናቸዉም ተፋሰስ ለማካሄድ የሚታቀዱ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በተፋሰሱ በሚገኝ የዓሳ ሀብት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የማያደርሱ መሆናቸዉ በቢሮዉ መረጋገጥ አለበት፡፡

5. በክልሉ ዉስጥ በቢሮዉ ካልተፈቀደ በስተቀር ማንኛዉንም ህይወት ያለዉን የዓሳ ዝሪያና ሌሎች የዉሃ ዉስጥ እንስሳትና ዕፅዋትን ከአንድ የዉሃ አካል ወደ ሌላ የዉሃ አካል ማሰራጨት ወይም ማዘዋወር ክልክል ነዉ፡፡

**7. የዓሳ ሀብትን በኮንሴሽን ስለመስጠት**

ቢሮዉ በተዋረድ ባሉት መዋቅሮች ጋር በማጥናት አንድ የዉሃ አካል የዓሳ ሀብትን ለአንድ ወይም ለብዙ ሰዎች በኮንሴሽን መስጠት ይችላል፡፡ የአሰጣጡም ሁኔታ ይህን ደንብ ለማስፈፀም በሚወጣው መመሪያ ላይ ይወሰናል፡፡

**ክፍል ሦስት**

**ዓሳ ስለማልማት**

**8. የዓሳ ግብርና ልማት**

1. ማንኛዉም ሰዉ በክልሉ ዉስጥ የዓሳ ዝሪያዎችን ለንግድ ለማርባት ሲፈልግ ከቢሮዉ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡ ፈቃዱም የሚሰጠዉ ከዚህ በታች የተመለከቱት ሁኔታዎች ሲሟሉ ይሆናል፡-

ሀ. ለተቋሙ የሚሆን በቂ መሬት መኖሩ ከሚመለከታቸዉ መዋቅሮች ሲረጋገጥ፡

ለ. ለተቋሙ የሚያስፈልግ በቂ ዉሃ ስለመኖሩና ለመጠቀም ስለመቻሉ አግባብ ካለዉ መንግስታዊ አካል ድጋፍ ሲያገኝ፡

afi’riro,

C) Uurrinsanni qulxu’mete ceatto uurrinsha qooxeessa daaffannokkita woy layyote heedhanno way bissara leeltanno qulxu’mete sirchi aananna xaphoomu layyote akati aana jaddo iillishanokkiha ikkassi buunxiro ikkanno.

2. Tantanantinoti Qulxu’mete gibrinni uurrinsha giddo Qulxu’mete xisso kalaqante qooxxeessu way bissa taraabbannonna jawa gawajjo iillishshanno yine ammaniro biirote uurrinsha cufa woy ashshaga dandiitanno.

3. Qulxu’mete gibrinninna qulxu’mete gibrinni uurrinsha ijaarsanna horoonsi’nanni gara lainohunni biiro tenne wodho loosu aana hosiisate fushshitanno biddissi aana hasiishu garinni gumula danddiitanno.

## Gafa shoole

## Qulxu’mete Laalchi Qixxaawonna Amadooshshe La’anno Hajubba

### 9. Qulxu’mete Laalchi Qixxaawonna Amadooshshe

1. Qulxu’mete laalchi qixxaawo, amadooshshe, gamba assa, duunanna tuqisate looso loosanno loosaassine:-

   a) Ayeeno tarawaano xibbinninna bisu aana leeltanno madanni keeraancho ikkasi hakimetewiinni buuxote taje amada heedhannonsa,

   b) Bisonsanna loosu uduuninsa keeranchimma agarantinoha ikka noosi.

ሐ. የሚቋቋመዉ የዓሳ ግብርና ተቋም አከባቢን የማይበክል ወይም በተፋሰሱ ባሉ የዉሃ አካላት በሚገኙ የዓሳ ዝሪያዎች ላይና በጠቅላላዉ በተፋሰሱ ሥነ-ምህዳር ላይ ጉዳት የማያደርስ መሆኑ ሲረጋገጥ ይሆናል፡፡

2. በተቋቋመዉ የዓሳ ግብርና ተቋም ዉስጥ የዓሳ በሽታ ተከስቶ ወደ አከባቢዉ የዉሃ አካላት ሊዛመትና የከፋ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል ተብሎ ከታመነ ቢሮዉ ተቋሙን መዝጋት ወይም ማሸግ ይችላል፡፡

3. የዓሳ ግብርናና የዓሳ ግብርና ተቋም ግምባታና አጠቃቀምን በተመለከተ ቢሮው ይህን ደንብ ለማስፈፀም በሚያወጣው መመሪያ ላይ እንዳስፈላጊነቱ ሊወሰን ይችላል፡፡

## ክፍል አራት

## የዓሳ ምርት ዝግጅትና አያያዝን የሚመለከቱ ጉዳዮች

### 9. የዓሳ ምርት ዝግጅትና አያያዝ

1. ከዓሳ ምርት ዝግጅት፣ አያያዝ፣ አሰባሰብ፣ ማከማቸትና ስርጭት ስራዎችን የሚሰሩ ሠራተኞች፡-

   ሀ. ከማንኛዉም ተላላፊ በሽታና ከሰዉነት ቁስለት ነፃ ስለመሆናቸዉ ከሀኪም ማረጋገጫ መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡

   ለ. ሰዉነታቸዉና የሥራ ልብሳቸዉ ንጽህናዉ የተጠበቀ መሆን አለበት፡፡

2. የዓሳ ምርት ዝግጅት፣ አያያዝ፣ አሰባሰብ፣ ማከማቸትና ስርጭትን በተመለከተ

2. Qulxu'mete laalchi Qixaawo, amadooshshe, gamba assa, duunanna tuqisa la'inohunni
   a) Way bissa qaccenna qooxeesira assinanni laalchu qixxaawo caalu noo dargubbara woy tenne hajora yine qixxeessinoonni caalira assa noosi.
   b) Qulxu'me hirranni kifile ikkadu arrishshote caabbicho eessannowanna hashsha hirranniha ikkiro ikkadu korreentete caabbichi hee'ra noosi.
   c) Qulxu'me hirranni suuqqara wole uduunne duunna, hiranna mini saada giddoonni saysa hoollonnite.

**10. Taje Aate Gadacho**

1. Qulxu'mete jiro latishshi agarooshshinna horoonsishshi ledo amadamino looso loosannohu ayno konni loosira loosate bobbahino manchi loososi lainohunni qulxu'mete jiro harunsonna irko assanno loosu minira taje aate gadacho noosi.
2. Biiro konni quwira cinaancho quwa 1 garinni gamba assitino taje keenatenninna qixxeessatenni hundaseenni noo tantanoranna wolootu horoonsi'raanora iillitanno gede assitanno.

**Gafa Onte**

**Wodho Jeefisiisannire**

**11. Qulxu'mete Jiro Harunsaancho Soma**

1. Biironna worooseenni noo tantanubba qulxu'mete jironna woloota way giddo saadanna mu'ro gashshatenna agarate biilloonyi noonsahura Qulxu'mete jiro harusannoha gaamatenni tenne wodho

ሀ. በዉሃ አካላት ዳሪቻዎች አከባቢ የሚደረግ የምርት ዝግጅት በጥላ ቦታዎች ወይም ለዚሁ ተብለዉ የተዘጋጁ መጠለያዎች ማከናዎን አለበት፡፡

ለ. ዓሳዉ የሚሸጥበት ክፍል በቂ የፀሐይ ብርሃን የሚያስገባ እና በምሽት የሚሸጥ ከሆነ በቂ የኤሌክትሪክ ብርሃን መኖር አለበት፡፡

ሐ. በዓሳ መሸጫ ሱቆች ሌሎች ዕቃዎችን ማከማቸት፣ መሸጥ እና የቤት እንስሳት እንዲዘዋወሩ ማድረግ የተከለከለ ነዉ፡፡

10. መረጃ የመስጠት ግዴታ

1. ከዓሳ ሀብት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም ጋር ተያያዥነት ያለዉን ስራ የሚሰራ ማንኛዉም በዚህ ስራ የተሰማራ ሰዉ ስራዉን በተመለከተ የዓሳ ሀብቱን ለሚቆጣጠረዉ መስሪያ ቤት መረጃ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡
2. ቢሮው በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሰረት የሰበሰባቸውን መረጃዎች በመገምገምና በማዘጋጀት በስሩ ላሉ መዋቅሮችና ለሌሎች ተጠቃሚዎች እንዲደርሱ ያደርጋል፡፡

**ክፍል አምስት**

**ደንቡን ስለማስፈፀም**

11. የዓሳ ሀብት ተቆጣጣሪን ስለመሰየም

1. ቢሮውና በተዋረድ ያሉ መዋቅሮች የዓሳ ሀብትና ሌሎች የዉሃ ዉስጥ እንስሳትንና እጽዋትን የማስተዳደርና የመጠበቅ ኃላፊነት ስላለባቸዉ የዓሳ ሀብት ተቆጣጣሪን

jeefisantanno gede assate gadacho noonsa.

2. Sommannihu Biirotenna deerru deerrunku noo tantanubba kaima assatenni ikkanno.

## 12. Qulxu'mete Jiro Harunsanchi Gadacho

Ayeeno qulxu'mete jiro harunsaanchi:-

1. Xa'minannisi yannara qulxu'mete jiro harunsaancho ikkasi xawisano taje leellishshate seerunni ikkinoha ayimmasi leelishshanno taje leellisha noosi.
2. Amandoonni qulxu'me, woshshaandanni uduunnicho woy wole uduunni dananna bikka amadantinonna qulxu'me hirantinota woy hunnooni barra hattonno hirotenni afi'noonni woxi bikka xawisanno darasanya amadamino manchira uynanni.
3. Tenne wodho garinni amandoonninna dikkote shiqishate ikkitanno ayee qulxu'me horote gobbaanni ikkitanokki gede gargarate qulxu'me amandoonni manchi noo qooxeessa yannate dikkote waagira seeru garinni hirranni gede assanno.
4. Tenne wodho garinni amandoonni woshshaandanni uduunnicho woy hodhinsanninna duunnanni uduunnichonna woloota uduunne yoo uyna geeshsha qorophotenni keeshshanno gede assanno.

## 13. Halamate Gadacho

Tenne wodhora xawinsoonni hajubba aana dhaaddotenni ikko dhaaddiweelo doogonni hajo la'annoosi aye manchino wodho loosu aana hosiisa lainohunni halamate gadacho noosi.

በመመደብ ይህ ደንብ ተፈፃሚ እንዲሆን የማድረግ ግዴታ አለባቸዉ፡፡

2. አሰያየሙም የቢሮዉንና የየመዋቅሩን አደረጃጀት መሰረት አድርጎ ይሆናል፡፡

## 12. የዓሳ ሀብት ተቆጣጣሪ ግዴታዎች

ማንኛዉም የዓሳ ሀብት ተቆጣጣሪ፡-

1. በሚጠየቅበት ጊዜ የዓሳ ሀብት ተቆጣጣሪ መሆኑን ለማሳወቅ ህጋዊ የሆነ መታወቂያ ማሳየት አለበት፡፡
2. የተያዘ ዓሳ፣ የማስገሪያ መሳሪያ ወይም ሌላ ዕቃ ዓይነትና መጠን የተያዘበትንና ዓሳዉ የተሸጠበትን ወይም የተወገደበትን ቀን እንዲሁም ከሽያጭ የተገኘዉን ገንዘብ መጠን የሚገልጽ ደረሰኝ ለተያዘበት ሰዉ ይሰጣል፡፡
3. በዚህ ደንብ መሰረት የተያዘና ለገበያ መቅረብ የሚችል ማንኛዉንም ዓሳ እንዳይበላሽ ለመከላከል ዓሳዉ የተያዘበት ሰዉ ባለበት በአካባቢዉ በወቅቱ የገበያ ዋጋ በህጋዊ መንገድ እንዲሸጥ ያደርጋል፡፡
4. በዚህ ደንብ መሰረት የተያዘ የማስገሪያ መሳሪያን ወይም ማጓጓዣና ማከማቻ ቁሳቁሶችንና ሌሎች ዕቃዎችን ፍርድ እስኪሰጥባቸዉ ድረስ በጥንቃቄ እንዲቆዩ ያደርጋል፡፡

## 13. የመተባበር ግዴታ

በዚህ ደንብ በተነሱ ጉዳዮች ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚመለከተዉ ማንኛዉም ሰዉ ደንቡን ከማስፈፀም አንፃር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

## Gafa Lee

## Babbaxxitino Woro

**14. Qoricha**

Tenne wodhora worroonni qorowo sainohu ayee manchi Itophiyu Federaalete Dimokiraasete Rippubilike Qulxu’mete Jiro Latishshinna Horoonsishshi Lallawi Kiiro 315/1995 quwa 16 nna 17 worroonni qorichi jeefamannoha ikkanno.

**15. Loosu Aana Hossannokki Seerubba**

Tenne wodho ledo kiphi yitannoti ayee wodho, biddissi woy rosichi tenne wodhonni hanqafantino hajubba aana jeefishshu dihee’rannonsa.

**16. Biddissa Fushshate Biilloonye**

Qoqqowu Saadate Jiro Latishshi Biiro tenne wodho jeefisiisate dandiisiissanno biddisuwa fushsha dandiitanno.

**17. Wodho Loosu Aana Hossanno Yanna**

Tini wodho Qoqqowu Jeefisiisaanote Amaale Mine wonsini barri Ella 8//2016 M.D hanaffe loosu aana hossanno.

**Desta Ledamo**

**Sidaamu Dagoomi Qoqqowi Mootimma Pirezidanticha**

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**14. ቅጣት**

በዚህ ደንብ የተደነገገዉን የተላለፈ ማንኛዉም ሰዉ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የዓሣ ሀብት ልማትና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር ፫፻፲፭/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፲፮ እና ፲፯ የተጠቀሱ ቅጣቶች ተፈጻሚ ይሆኑበታል፡፡

**15. የተሻሩና ተፈፃሚነት ስለሌላቸው ሕጎች**

ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛዉም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልምድ በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረዉም፡፡

**16. መመሪያ የማዉጣት ስልጣን**

የክልሉ እንስሳት ሀብት ልማት ቢሮ ይህንን ደንብ ለመተግበር የሚያስችሉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

**17. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት ከፀደቀበት ሰኔ ፰ ቀን ፳፻፲፮ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ደስታ ሌዳሞ**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር**